# የዓለም-አቀፍ ስምምነቶች በአዕምሯዊ ንብረት በተለይም ከበርን እና ከፓሪስ ኮንቬንሽን አንፃር

## ግሎባል ሆቴል

ሚያዚያ 28 ቀን 2009 ዓ.ም.

- የስብሳበው አጀንዳ/ርዕሰ-ጉዳይ፡ የዓለም-አቀፍ ስምምነቶች በአዕምሯዊ ንብረት በተለይም ከበርን እና ከፓሪስ ኮንቬንሽን አንፃር
- ጽሑፍ አቅራቢ፡- አቶ አማን አሠፋ
- አወያይ፡- አቶ ኤርሚያስ የማነብርሃን - ከኢትዮጵያ የአእምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት የንግድ ምልክት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር
- የስብሰባው ቦታ፡-ግሎባል ሆቴል
- በአውደጥናቱ ላይ የተገኙ፡- ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት መ/ቤት ተወካዮች፣ ጠበቆች፣ የማኅበሩ አባላትና ሌሎችም
- የአውደጥናቱ ቀን፡- ሚያዚያ 28 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 እስከ ከቀኑ 6፡30 ሠዓት

<u>አቶ ቴዎድሮስ ምህረት- የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዝዳንት</u>



የማኅበሩ ፕሬዝዳንት የእንኳን ደህና መጣችሁ እና የመክፈቻ ንግግር በማድረግ የስብሰባውን በይፋ መከፈት በማብሰር የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከተለያዩ ባለድርሻ የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ የእርስ በእርስ መማማሪያ መድረክ በመፍጠር እና ሥነ-ሕግን በማሳደግ የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የተከበሩ አቶ አባይነህ ተላከ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሳይንስ መገናኛና ቴክኖሎጂ

ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ጥሪያችንን አክብረው በመገኘታቸው ምስጋናቸውን አቅርበው በመጨረሻም የስብሳበው ተሳታፊዎች በሚቀርበው ጽሁፍ ላይ ሃሳብ አስተያየታችሁን በመስጠትና ተሞክሮአቸውን በመግለፅ እውቀትና ልምዳቸውንያካፍላሉ የሚል እምነት እንዳላቸው ለተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡ በዕለቱ የተሰናዳው ትምህርታዊ መድረክ ማኅበሩ ያዘጋጀ ሲሆን አቶ አማን አሠፋ የመወያያ ጽሑፉን ከማቅረብ ባሻገር ለስብሰባው የሚያስፈልጉ ወጪዎችን በመሸፈን ስፖንሰር ያደረገ በመሆኑ ሊመሰገን እንደሚገባ'ያመለከቱት አቶ ቴወድሮሰ ከአእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ጊዜያቸውን ሰውተው አወያይ ለመሆን ፈቃደኛ በመሆን የመጡጥን አቶ ኤርሚያስ የማነብርሃንንእንዲሁም የማኅበሩን ጥሪ አክብረው በአውደጥናቱ ላይ የተገኙ ባለሙያዎችን በማመስግን እና የዕለቱ ውይይት የተሳካ እዲሆን በመመኘት የመክፈቻ ንገግራቸውን አብቅተዋል፡፡

## <u>አቶ ኤርሚያስ የማነብርሃን - አወያይ</u>

አቶ ኤርሚያስ የማነብርሃን የሳይንስ መገናኛና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑትን ክቡር አቶ አባይነህ ተለካ እንዲሁም ታዳሚ የሕግ አማካሪና ጠበቆችን የእንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኂላ የመወያያ ጽሑፉን የሚያቀርቡት አቶ አማን አሰፋ መሆናቸውን ጠቅሰው የዕለቱ ርዕሰ-ጉዳይም የዓለም አቀፍ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ስምምነቶች በተለይም የበርን እና የፓሪስ ስምምነት ላይ ትኩረት የሚደረግ መሆኑንለተሳታፊው አስገንዝበዋል፡፡ አወያዩ አክለውም ኢትዮጵያ እነዚህን ሁለት ስምምነቶች ያልፈረመችና የሕን አካል ያላደረገች መሆኑን ገልፀው ኢትዮጵያ ከአእምሯዊ ንብረት የአለም-አቀፍ ስምምነቶች መካካል የWIPO፣ የናይሮቢ የኦሎምፒክ ምልክቶች እና የማራካሽ ስምምነት የፈረመች መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በመጨረሻም ለአቶ አማን አሠፋ መድረኩን አሳልፈው የሰጡ ሲሆን ጽሑፍ አቅራቢውም ይመከተለውን አስቀምጠዋል፡፡

## <u>አቶ አማን አሠፋ - ጽሑፍ አቅራቢ</u>

በዕለቱ የተያዘው የመወያያ ርዕስ የዓለም-አቀፍ ስምምነቶች በአዕምሯዊ ንብረት በተለይምከበርን እና ከፓሪስ ኮንቬንሽን አንፃር የሚል መሆኑን ገልፀው እነዚህን ሁለት ስምምነቶች ሀገራችን ያልፈረመች ሲሆን ፈራሚ አባል ሀገር ለመሆን የሚደረግ ጥረትና እንቅስቃሴ በመንግሥት በኩል ካለ ይህ ከመሆኑ በፊት መጠነ ሰፊ ዳሰሳ ማድርግ አስፈላጊጉዳይ እንደሆነ በመጠቆም ስምምነቶች ጥልቅ ጥናትና ምርምርን የሚሹ ናቸው ብለዋል፡፡ በስምምነቶቹ ላይ የሚነሱ

ሃሳብና ክርክሮችመጀመሪያ እንጂ መጨረሻ አይሆንም የሚል ግምት እንዳላቸው የገለፁት ፅሁፍ አቅራቢው የስምምነቶቹን አንኳር አንኳር ነጥብ በማንሳት ስለጉዳዩ sensitize በማድረግ አስተዋፅዖ ለማበርከት እንጂ ስለ ኮንቬንሽኖች ጠቃሚነት ወይንም ጎጂነት (ጎጂም ከሆኑ ከነማርከሻቸው) ሙሉ ዳሰሳ አድርጎ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አለመሆኑን አንስተዋል፡፡

የውይይቱ ዓላማና ግብ በዋናነት መስኩ እጅግ ሰፊና በተለይም ደግሞ አሳሳቢ መሆኑን ማስጨበጥ እንደሆነ ጠቅሰው እነዚህ ስምምነቶች የ19ኛ ክፍለዘመን ኮንቬንሽኖች ሲሆን እኛ እነዚህ ሕግጋቶች ላይ በ21ኛ ክፌለዘመን ላይ ሆነን መነጋገራችን ትልቅ advantage ያለን መሆኑን እንደ አዳጊ አፍሪካዊ አገር - ከሌሎች አገሮች ስህተቶች እና ሴኬቶች ለመማር እድል እንደሚፈጥርልን የጠቆሙት አቶ አማን ሌሎችታዳጊ አገሮች ፓሪስ እና በርንን ሲቀበሉ በቀኝ ገዢዎቻቸው ታዘው እነደነበርናጥቅምና ጉዳቱ ከሀገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ ምንድን ነው የሚለውን በጥልቀት ለመመርመር እድሉንም አላገኙም ነበር ብለዋል፡፡

ብልህ ሰው ከሌላው ስህተት ይማራል በማለት በዘርፉ የሚነሱ መሠረታዊና ዘርፈ ብዙ ጥያቄዎችን ጽሁፍ አቅራቢውያነሱ ሲሆን ከነዚህም መካከል የነዚህ ስምምነቶች ሥርዓቱ እንዴት ነው የሚሰራው? ስርዓቱ በራሱ (ሌሎች አለማቀፍ የንግድ እና ሌሎች ግንኙነቶችን ግምት ውስጥ ሳያስገባ) ኢትዮጵያን ይጠቅማል ወይስ ይጎዳል?አይጠቅምም ከተባለ ወጪያችን ስንት ነው? ወጪያችንንለመቀነስና በየኮንቬንሽኖቹ ውሥጥ የተሰገሰጉትን ጥቃቅን ጥቅሞች እንዴት ነው የምንጠቀምባቸው?በራሱ የማይጠቅመን ሆኖ እንኳ ቢገኝ ለምንድን ነው ልንገባ የምንፈልገው ወይንም የምንገደደው? በተለይም ደግሞ በዚህ እንኳ ብንጎዳ ወደነዚህ ስምምነቶች ስንገባ የምናዳብራቸው እና የሚጠቅሙን ሌሎች ግንኙነቶች አሉ ወይ - ጥቅማቸውስ ምን ያህል ነው?ወዘተ አንስተው ስምምነቶቹን የፈረሙ ብዙ ሀገራት በመሆናቸው ከኛ ሀገር ኢኮኖሚ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ከሆኑ አባል ሀገራት ብዙ ተሞክሮዎችን መቅሰም እንሚገባን ጠቁመዋል፡፡

አቶ አማን አእምሯዊ ንብረት ሰፊ ዲሲፐሊን መሆኑን ገልፀው በእለት ተለት ኑሯችንን የአእምሯዊ ንብረተቶች impact በሚያደርጉን ነገሮች የተመላ መሆኑ ለምሳሌ ቴክኒካዊ ይዘት ያላቸው ፈጠራዎች፣ መድሃኒት፣ ሶፍትዌር፣ ማምረቻ መሳሪያዎች፣ ሜካኒካዊ ይዘት ያላቸው መሳሪያዎች እና የዕለት ተዕለት ቁሳቁሶችና ኑሮ ማቅለያ መሳሪያዎች፣ ሰፋፊ የግብርና

ጠቀሜታ ያላቸው የኬሚካል እና ሌሎች ምርቶች፣ የተሻሻሉ ዝርያዎች፣ ሞባይል ስልክ፣ ኮመፒውተር፣ መኪኖች፣ አውሮፕላሎች፣ የከተማ እና አገር አቋራጭ ባቡሮች፣ የነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ እና ትራፊክ መቆጣጠሪያ ሲስተሞች፣ በየተለያዩ ስራ መስኮች ለየመስኩ በተለየ ሁኔታ የተሰሩ ስራ ማቅለያ ወይንም አጋዥ ሶፍትዌሮች - ለሂሳብ ስራ፣ ለሕግ ስራ፣ ለህክምና ስራ፣ ለላይብረሪ፣ ለመንግስት አስተዳደር (የግብር፣ የንግድ ምዝገባ)፣ ለባንክ ስራዎች (ገንዘብ መክፈል እና መቀበል፣ ማንኛውም የተፃፈ ነገር፣ ሙዚቃ፣ፊልም፣የመድረክ ስራዎች (ቴያትር ወዘተ)፣ ውዝዋዜ እና ዳንስ፣ ስነ ጥበብወዘተ የአእምሮ ንብረት ጉዳይ የሚነሳባቸው ናቸው። የበርን ኮንቬንሽን አባል ሆንን ማለት ይህ ሕይወታችንን impact በሚያደርግ ጉዳይ ተስማማን ማለት እንደሆነ የገለፁ ሲሆን የsoftware penetration በሀገራችን ሲታይ እጅግ በጣም ውስን እንደሆነ ጭምር አውስተዋል።የአእምሮ መብት ሕግ rhetoric እና mainstream thoughts የፕሮሞተሮቹን ጥቅሞች ብቻ ታሳቢ ያደረጉ እና ባሉበት መልኩ የግድ ሁሉንም የሚጠቅሙ አለመሆናቸውን ካላቸው ልምድና ተሞክሮ ሲገልፁ መነሻ ያደረጓቸው መሰረታዊ ኢኮኖሚያዊ እውነታዎች እና ገፅታዎች መኖራቸውንና ያለጥርጥር እነሱ እውነታዎች እና ገፅታዎች እኛን አይወክሉም ብለዋል አቶ አማን።

የአእምሯዊ ንብረት መብት ዓላማ ባለመብቱ ሌሎች ሰዎችን የመከልከል እንዲሁም ለባለመብቱ እውቅና መስጫ መንገዶች ናቸው ያሉት አቶ አማን እነዚህ መብቶች ኢኮኖሚያዊ ፊይዳ እንዲሁም ከሞራልና ከተፈጥሮ ጋር ቁርኝት እንዳላቸው አንስተዋል። ከነዚህ ዓላማዎች ባሻገር ፈጠራ እንዲበረታታ እና የፈጠራ ሥራዎች ይበልጥ እንዲስፋፉ የራሱን አስተዋፅዖ ያበረክታል።ሌሎችን ማበረታታት የሚባለው ግብ አንጒነቱን ግምት ውስጥ በማስገባት አንዱ መብቱ ተጠብቆለት ጥቅም ሲያገኝ ሌላው ይበረታታል የሚለው ሃሳብይህንን ግብ ሕጉ ሊያሳካው የሚችለው በእርሳቸው እምነት መጀመሪያ የፈጠራ እንቅስቃሴው እና ባህሉ ኖሮ ጥበቃው የላላ በመሆኑ ምክንያት በስርቆት ፍርሃት ከፈጠራ ስራ የራቀ ማህበረሰብ ውስጥ እንደሆነና የፈጠራ ባህል እና ክህሎት በሌለበት ማህበረሰብ ውስጥ ባህሉን እና ክህሎቱን በመፍጠር ረገድ ህጉ ሊኖረው የሚችለው ሚና ዝቅተኛ መሆኑን ምናልባትምሕጉን ከመደንገግ አልፎ የፈጠራ ባህል ለማዳበር ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ የግድ ሊል ይችላል ብለዋል።ህጉን ማስፈፀም የሚያስችል ተቋማዊ ብቃትም ያስፈልጋል። ሲስተሚክ clogging በየቦታው ካለ ይህ ህግ አላማውን ሊያሳካ ፈፅሞ እንደማይችልና የአእምሮ ፈጠራ መብት

ባህርይ - ሌሎችን ማስከልከያ መሳሪያ ነው እንጂ ባለመብቱ የፈጠረውን ነገር እንዴት አንደሚገለገልበት የሚያወሳ አለመሆኑንና ለሌሎች ማስጠንቀቂያ መሆኑን አክለው ገልፀዋል፡፡

ጽሑፍ አቅራቢው ይህን ካስቀመጡ በኋላ በቀጥታ ወደ ስምምነቶቹ ዳሠሳ የገቡ ሲሆን በቅድሚያ ያቀረቡት የበርን ኮንቬንሽንን የሚመለከት ነው፡፡ ወደ ስምምነቱ ገለፃ ከመግባታቸው በፊት እርሳቸው የሚያቀርቡት ሁለቱን ስምምነቶች ሆኖ የድንጋጌዎቹን ወጪ መቀነሻ መንገዶች ወይም ሥርዓቶች ላይ የሚያተኩሩ እና በሌሎች ስምምነቶች ላይም አንድ አንድ ሊታሰብባቸው የሚገቡ ነጥቦችን አቅጣጫ ለመጠቆም የሚሞክሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡



የበርን ኮንቬንሽን አመጣጥ ወይም አፈጣጠርን በተመለከተ የዓለምአቀፍ የንግድ ግንኙነት መዳበርና የኢንደስትሪው አብዮት ከፍተኛ በሆነበት ጊዜ መሆኑን፤ የአውሮፓ ሀገራት እርስ በእርስ እንዲሁም ከሰሜን አሜሪካ ጋር የነበራቸው ግንኙነት እንዲዳብር ያደረገው የአንዱ ሀገር ዜጋ ሥራዎች በሌላኛው ሀገር ጥበቃ የመሻት፣ የአእምሮ ውጤት ጥበቃ በመስጠት ስርቆትን የማጥፋትና በወቅቱ የነበረውን ባሕላዊና የንግድ ትስስር ይበልጥ ለማሳደግና ከአደጋ ለመጠበቅ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

የበርን ኮንቬንሽን መሠረታዊ ይዘቶች (minimum standards) በማስቀመጥ የharmonization ይዘት እና ቁምነገር ያለው መሆኑን ጠቅሰው ከባለመብት ይልቅ ደራሲ ላይ ያተኮረ መሆኑን

እና ጥበቃ የሚደረግላቸው የስራ ዓይነቶችለመጀመሪያ ጊዜ የተሰሩ (ጽሁፍ፣ ንግግር፣ የመድረክ ስራዎች፣ ውዝዋዜ ስልት፣ የሙዚቃ ዜማ፣ ፊልም፣ ስነጥበብ ስራዎች (ስዕል፣ ንድፍ፣ ቅርፅ …) የህንፃ ዲዛይን፣ የፊደላት ቅርፅ፣ ፎቶግራፍ፣ የቁሳቁስ ዲዛይን እና ንድፎቻቸው፣ ስዕላዊ መግለጫዎች፣ ማፖች፣ ሶስት - ዳይሜንሽን ያላቸው አንዳንድ ስራዎች፤ዴሪቬቲቭ ስራዎች - በመነሻዎቹ ላይ ያለ መብት ሳይነካ፤ የስራዎች ስብስብ እና መድብሎች ወዘተ እንደሆኑ ዘርዝረዋል።

በኮንቬንሽኑ መሠረት ጥበቃ የሚያገኘው ማነው የሚለውን በሚመለከት የስራውአመንጪ ሆኖቢታተምም ባይታተምም የአባል አገር ዜጋ ያመነጫቸው፤ ዜጋ ባይሆንም በአባል አገር ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመ ወይንም አባል ካልሆነ አገር ተሰርቶ በ30 ቀናት ውስጥ አባል በሆነ አገር ውስጥ ያሳተመ (የሰራ ብቻ ሳይሆን ማለት ነው)፤ ፊልም ከሆነ - ሰሪው አባል የሆነ አገር ላይ ዋና ፅ/ቤቱ ያለ፤ ህንፃ ከሆነ - አባል የሆነ አገር ላይ የተገነባ እንደሆነ በዝርዝር አስረድተዋል።

የበርን ስምምነት ፈራሚ አባል ሀገር ከተኾነ ጊዜ ጀምሮ ከሌሎች ሀገር ለሚመጡ ሥራዎች automatically ጥበቃ መስጠት ይጀምራል። ለምሳሌ አንድ የህንድ ሙዚቃ ልክ ታትሞ ሲለቀቅ ወዲያኑ በሌሎች ሀገራት ጥበቃ ይቸረዋል-ባለመብቱ ጥበቃ እንዲሰጠው ማመልከት ሳይጠበቅበት ብለዋል። There is no formality and no prior application needed. ስምምነቱ ምንም ዓይነት አስተዳደራዊ ቅድመ ሁኔታዎች ፈፅሞ እንዳይኖሩ ይደነግጋል። በኮንቬንሽኑ ጥበቃ የሚደረግለት ስራው ከመነጨበት አገር ውጪ በሌሎች የኮንቬንሽኑ አባል አገር ላይ ጥበቃ ማስገኘት ነው። ስለሆነም ከመነጨበት አገር ስለሚያገኘው ጥበቃ ሳይሆን ሌላ አገር ሲወሰድ ስለሚጠይቀው ጥበቃ እንደሆነ አብራርተዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የፓሪስ ስምምነት በተቃራኒው formal application ይፈልጋል ስለሆነም የሁለቱ ስምምነቶች impact የተለያየ ነው ብለዋል።

የበርን ኮንቬንሽን ሲጀመር የተፈረመው በ10 ሀገራት በ1886 ማለትም በአድዋ ጦርነት ዋዜማ እንደሆነና የስምምነቱ አስፈላጊነት ለeconomic integration ነው ብለዋል። የበርን ኮንቬንሽን ከሌሎች ዓለምአቀፍ ስምምነቶች አንፃር ብዛት ያለው ድንጋጌዎችን በዝርዝር ያስቀመጠ ነው።የኮንቬንሽኑን አሰራር ለመረዳት ዝርዝር ድንጋጌዎቹን ከማውሳት ይልቅ ኢትዮጵያ አባል ብትሆን እና ያገሪቱን ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት የሚከሰቱትን ህጋዊ ክስተቶች በምሳሌ

ማሳየት ለዚህ ስብሰባ አላማ የተሻለ መሆኑን ጠቁመው ግምት ውስጥ የምናስገባቸው የኮንቬንሽኑ ደንቦች ጥበቃ የሚደረግላቸው ስራዎች፦

1. ናሽናል ትሪትመንት፣
2. ቴሪቶሪያሊቲ፣ እና
3. ካንትሪ ኦፍ ኦሪጂን ናቸው።

እነዚህ የኮንቬንሽኑ አንኳር እና ምሰሶ ደምቦች ናቸው።ስለሆነም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ሰው ያመነጨው ስራ (የትም ቢኖር) እናም ስራዉን ሰርቶ ሲጨርስ (ማሳተም ሳያስፈልገው) አየርላንድም ሆነ ጓቴማላ፣ እንዲሁም ኳታር፣ አሜሪካ፣ ኢንግሊዝ፣ ጀርመን፣ ጣሊያን፣ ብራዚል፣ ኮትዲቯር፣ ቡላጋሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኒካራጉዋ እና ሞሮኮ ይከበራሉ ማለት ነው - ለዚህ ጥሩ ምሳሌ እንግሊዝ የሚኖር ኢትዮጵያዊ የሳለው ስዕል ካለ እና ዱባይ ውስጥ አለፍቃዱ ቢባዛ እና ቢሸጥእንግሊዝ በመኖሩ ብቻ ኢትዮጵያ አባል ባትሆንም ዱባይ ሄዶ መክሰስ ይችላል በማለት አስረድተዋል። ስለሆነም በፈራሚ አባል ሀገር permanently and habitually reside ማድረግ ብቻ ዜግነት ሳይጠየቅ ጥበቃን ያጎናፅፋል።

ሀገራችን የበርን ኮንቬንሽን አባል ሀገር ብትሆን አንድ ኤርትራዊ (የበርን አባል አይደለችም) ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሳተመው ስራ (ማሳተም ትርጉሙ ተለይቶ ተቀምጧል) ኢትዮጵያ ውስጥ በማሳተሙ ብቻ ከላይ በተቀመጡት አገሮች ዘንድ ጥበቃ የሚያገኝ መሆኑን ወይንም ኤርትራዊው አስመራ ለመጀመሪያ ጊዜ አሳትሞ መልሶ ደግሞ በ30 ቀናት ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሳተመዉ እንዲሁ ጥበቃ የሚቸረው መሆኑን ጠቁመዋል። መደበኛ መኖሪያውን ኢትዮጵያ ውስጥ ያደረገ ኤርትራዊ እንደኢትዮጵያዊ ይቆጠራል፤ ስለሆነም አሜሪካ አገር ለጉብኝት ሄዶ የደረሰው ሙዚቃ ወይንም የፃፈው ወይንም ያሳተመው መጽሐፍ፣ ወይንም አሜሪካ የታየ የደረሰው ቴያትር ከላይ በተጠቀሱት አገሮች ጥበቃ ያገኛል።

በመሆኑም ነዋሪውም እንደ ዜጋ ጥበቃ ይሰጠዋል ማለት ነው ብለዋል። ፊልምን በሚመለከት ትንሽ የተለየ ድንጋጌ መኖሩን የጠቆሙት አቶ አማን ፊልሙን የሰራው ወይም ያዘጋጀው አካል headquarter ያለበት ሀገር አባል ከሆነ ጥበቃ ይደረጋል። ኢትዮጵያ ውስጥ በተመዘገበ ፊልም ሰሪ የተሰራ ፊልም ሆኖ ዳይሬክተሩ ወይንም ፕሮዲውሰሩ ዜግነቱ ጣልያናዊ ወይንም ኢትዮጵያዊ ወይንም ኤርትራዊ ወይንም የፈለገው ቢሆን ጥበቃ ይሰጠዋል ብለዋል። የሕንፃ ግንባታን በተመለከተ የአርኪቴክተሩ ዜግነት የትም ይሁን ሕንፃው የተገነባበት ሀገር አባል

ሀገር ከሆነ ጥበቃ እንደሚሰጠው ጠቁመው ለምሳሌ ኢትዮጵያ ፈራሚ ብትሆን ኢትዮጵያ ውስጥ የተገነባ ህንፃ አርኪትክቱ ስፔናዊ፣ ኢትዮጵያዊ፣ ህንዳዊ ወይንም የፈለገው ቢሆን ጥበቃ ይሰጠዋል ማለት ነው፡፡አመንጪዎቹ ኢትዮጵያውያን በሆኑ ሰዎች የተሰራ ስራ ሆኖ (ለምሳሌ ዜማ ደራሲው ኢትዮጵያዊ ሆኖ) ባለመብቱ ግን ፈረንሳይ ሀገር ያለ የሙዚቃ ኩባንያ ቢሆንም የኮንቬንሽኑ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል በማለት በምሳሌ በማስደገፍ አብራርተዋል፡፡

እነዚህ ከላይ የጠቀሱ ሰዎች ከላይ በተጠቀሱ አገሮች ዘንድ በኮንቬንሽኑ አማካኝነት ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ ይህም ማለት ለምሳሌ የትም ይታተም የትም አንድ አማርኛ ዘፈን ዱባይ ባለ የምሽት ክበብ ያለዜማ ደራሲው ወይንም ያለአቀናባሪው ፍቃድ (እነዚህ ሰዎች ኢትዮጵያን ሆነው) ወይንም ያለ ቅጂባለመብቱ ፍቃድ ቢዘፈን ባለመብቱ ዱባይ ሄዶ መብቱን ሲጠይቅ በኮንቬንሽኑ ለዜማ ደራሲዎች እና አቀናባሪዎች የተሰጡ መብቶችን ወይንም ከዚህ የሚልቅ ሆኖ ቢገኝ ደግሞ በኢሚሬትስ ህግ ለዜማ ደራሲዎች እና አቀናባሪዎች የተሰጡትን መብቶች ተገን አድርጎ ዱባይ ውስጥ ሊከስ እና ካሳ ሊጠይቅ እንዲሁም መልሶ እንዳይዘፈን፤ ህገወጥ ቅጂዎችሲባዙ የነበረ ከሆነም በተመሳሳይ መልኩ ቅጂዎቹ እንዲቃጠሉ መጠየቅን ጨምሮሊጠይቅ ይችላል በማለት አስገንዝበዋል፡፡ ይህ ሲሆንየኢሚሬትስ ህግ ግዙፍነትን የሚጠይቅ ከሆነ ይሄው ተከብሮ መሆን አለበት ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

ስራው መፅሃፍ ቢሆን እና በኢትዮጵያዊ የተደረሰ ከሆነ ዱባይ ውስጥ መከበሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን መጀመሪያ የታተመው ኢንግሊዝ ከሆነ ስራው ከእንግሊዝ የመነጨ ስራ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ስራ አመንጪ ሃገር እና ጥበቃ የተፈለገበት አገር ፅንሰ ሃሳቦች ለበርን አፈፃፀም ወሳኝ ፅንሰሃሳቦች ናቸው ብለዋል፡፡ አጋጣሚ ሆኖ አንድ ኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ነዋሪ በሆነ የእንግሊዝ ፓስፖርት ባለው ሰው የተፃፈ ስለኢትዮጵያ የቱሪስት መስህቦች የሚያትት መጽሐፍ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ ኒውዚላንድ እና አየርላንድ ውስጥ ለእንግሊዘኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ተብሎ ቢታተም እና ጀርመን ውስጥ በህገወጥ መንገድ ቢባዛ እና ቢሸጥ ስራው ኢትዮጵያ ውስጥ ኗሪ በሆነ ሰው የተሰራ ስለሆነ በጀርመን ህግ ጥበቃ ይቸረዋል ያሉት ፀሁፍ አቅራቢ ባለመብቱም ኮንቬንሽኑ ወይንም ከበለጠ ደግሞ ጀርመን የምትሰጠውን መብት ይጥይቃል፡፡ በኮንቬንሽኑ መሠረት ላይፍ ፕላስ 50 ዓመት እንደተጠበቀ ሆኖየሚያገኘው ጥበቃ ግን በጀርመን ህግ መሰረት ይሆናል፡፡አንድ ኤርትራ ነዋሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ ኤርትራ ውስጥ መፅሃፍ ቢያሳትም ስራው መነጨ የሚባለው ከኢትዮጵያ ሆኖ

ምናልባት ካናዳ ውስጥ ጥሰት ቢፈፀምበት ባለመብቱ የካናዳ ህግን ተገን አድርጎ መብቱ እንዲከበር መጠየቅ እንደሚችል አስረድተዋል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ምሳሌዎች መረዳት እንደሚቻለው የበርን ስምምነት አባል ስንሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ተሰርተው ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚቀሩ ሥራዎች ብቻ ነው ጥበቃ የሚሰጠው ምክንያቱም ወደ ሌሎች ፈራሚ አባል ሀገራት በተለያየ አግባብ የሚሄዱ ሥራዎች እና የሥራ አመንጪዎች ለሥራቸው ጥበቃ ይሰጣቸዋል በሚል አስረድተዋል፡፡ ኮንቬንሽኑ ሥራዎች ጥበቃ እንዲያገኙ ወደ ግዙፍነት መቀየርን (fixation) እንደቅድመሁኔታ አያስቀምጥም ብለዋል፡፡

የተለመዱት የኢኮኖሚ መብቶችማባዛት እና ማሰራጨት፤ መከወን፣ ማሳየት እና በተለያዩ መንገዶች ህዝብ ዘንድ እንዲደርስ ማድረግ (communication to public)፤የብሮድካስቲንግ መብት፣የመቀየር፣ ማቀናበር እና ማመሳሰል መብቶች፣የመተርጎም መብት፣የስነጥበብ ስራ እና ዋናው የማኒዩስክሪፕት መልሶ ሽያጭ ላይ የመካፈል መብት (ደራሲው ባገሩ መብቱ ከነበረው እና ጥበቃው በተሻተበት አገርም መብቱ ካለ) ወዘተ ሲሆኑ የሞራል መብቶችም አሉት ብለዋል፡፡የመብቱ እድሜ ደራሲው በሂወት እስካለ እና ከሞተም በኋላ ለ50 ዓመት የሚዘልቅ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ስለግጭት አፈታት በሚመለከት አንቀፅ 33 መሠረት የመብት ጥሰት ለሄጉ አለምአቀፉ ፍርድ ቤት (International Court of Justice) ሲሆን የICJ ሥልጣን ደግሞ በሀገራት ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ከመሆኑም በላይ የበርን ኮንቬንሽንን ስንቀበል የICJ ሥልጣን reserve ማድረግ የምንችል መሆኑ ተደንግጓል ተብሏል፡፡ በዚሁ ምክንያት እስካሁን ድረስ በዚህ ዐለምአቀፍ ፍ/ቤት በበርን ስምምነት ጋር የተያያዘ ኬዝ አለመኖሩን አስታውሰው የበርን እና የፓሪስ ስምምነቶች ስለግለሰቦች ወይም ሥራ አመንጪ ሰዎች እንጂ ስለሀገራት አይደለም የሚያወሩት ነገር ግን አንቀፅ 33 ስለ ፈራሚ አባል ሀገራት ነው ብለዋል፡፡

በርን አንዳንድ ስራዎች ጥበቃ ባይደረግላቸው የማይቃወም መሆኑን ለምሳሌ የመንግስት ሰነዶች እና ህጎች፣ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ንግግሮች ወዘተን ጠቅሰዋል፡፡ በርን የተወሰኑ መብቶች ላይ ስለሚደረጉ ገደቦች ጭምር የሚያወሳ ሲሆን እነዚህምየመጥቀስ ገደብ፣ ለትምህርት አላማ ሲባል፣ ዜናን ለመዘገብ ሲባል (የባለመብቱን ጥቅም አላግበባ ሳያጣብብ፣ ፍትሃዊ እስከሆነ እና አስፈላጊ በሆነበት ልክ) ወዘተ መኖራቸውንና በርን በርካታ ሌሎች

ተያያዥ፣ ለትርጉም የተጋለጡ እና ዝርዝር ነጥቦች ላይም የተለያዩ ኮፒራይትን የሚመለከቱድንጋጌዎች ያሉት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የበርን ኮንቬንሽን የሚመለከተው የሥራ አመንጪዎችን ብቻ ሲሆን ስለከዋኞች መብት፣ ስለየሙዚቃ/ሌሎች የድምፅ ምርቶች አሳታሚዎች መብቶችና ስለብሮድካስተሮች አያወሳም፡፡ ለከወኞች ጥበቃ የሚሰጠው የሮም ኮንቬንሽን ነው በማለት አብራርተዋል፡፡

የበርን አባል የመሆን ጠቀሜታን አስመልክቶ እንደማንኛውም የዓለምአቀፍ ስምምነት የአንድ ስምምነት ፈራሚ አገር ሲኮን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታው ስለሚኖረው እንደሆነ ጠቅሰው ስትራቴጂክ ጠቀሜታ ሲባል በበርንን ይዘት ብቻ ታጥረን እና አልያም ደግሞ ከበርን አጥር ውጪ ባሉ ሌሎች እሳቤዎች ምክንያት ሊሆን ይችላል ብለዋል፡፡ በዓለምአቀፍ ደራጃ ያለንን ኢሜጅ የተሻለ ሊያደርግ ወይም የውጭ ኢንቬስተሮች ሊስብ የሚችል መሆኑን ልናነሳ እንችላለን ብለዋል፡፡የበርን መነሻ ስራ አመንጪውን ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ተጠቃሚ ነች የምትባለው ባለመብቱ ማንም ቢሆን ማንም  በዋናነት በኢትዮጵያውያን ስራ አመንጪዎች የተሰሩ የስነፅሁፍ፣ ስነቃል፣ ስነጥበብ፣ ሙዚቃ፣ ቲያትርና ስራዎች (ሌሎችንም ጨምሮ) ወይንም ኢትዮጵያ ውስጥ የተገነቡ ህንፃዎች ዲዛይን ወይንም ኢትዮጵያ ውስጥ በተመዘገቡ የፊልም ስራ ድርጅቶች የተሰሩ ፊልሞች በሌሎች አገሮች ጥበቃ በማግኘታቸው ብቻ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ነገር ግን የበርን አባል ስንሆን በዜጎቻችን የተሰሩትን በሌሎች አገሮች ማስከበራችን ብቻ ሳይሆን የ166 አገሮች ዜጎች የሰሯቸው ስራዎችም ኢትዮጵያ ውስጥ ጥበቃን ለመስጠት ቃል በመግባት ነው፡፡ አለም ሁሉ የሰራውን ይህን ሁሉ ስራ ማለት ነው፡፡ስለሆነም ጥቅሙ በክፍያ የሚገኝ ነው እንጂ በነፃ የሚገኝ አይደለም ያሉት አቶ አማን ጥቅማችን ነው የሚበዛው ወይንስ ዕዳችን የሚል የሚል ጥያቄ አንስተዋል፡፡ይህንን ጥያቄ ለመመለስ መጠነ ሰፊ ዳሰሳዊ ጥናት ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ዋናው የጥናቱ ዓላማ የበርን አባል ብንሆን ኖሮ አገሪቱ ከውጭ ለምታስገባቸው የኮፒራይት ምርቶች እና ለቀጣይ ምርቶች (future production) በውጭ ምንዛሪ ምን ያክል ትከፍል ይሆን የሚለው እና ወደውጭ የምትልከው ደግሞ ምን ያህል የውጭ ምንዛሪ ታገኝ ነበር የሚል ነጥብን በዋናነት አንስተዋል፡፡እዚህ ላይ እንግዲህ አገሪቱ ለኢኮኖሚያዊ እድገቷ የሚያስፈልጉ የኮፒራይት ምርቶችስ አሉ ወይ የሚለው አብሮ መታየት አለበት፡፡ ለመዝናናት ከሚያስፈልጉ ምርቶች ውጪ (*ሙዚቃ፣ መዝናኛ፣ ፊልም፣ ውዝዋዜ፣ ስዕል እና የመሳሰሉት*) ለእድገት እጅግ ወሳኝ የሆኑ (indispensable) ምርቶችም የሚገኙበት መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም፡፡ አገሪቱ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ ኮምፒዉተሮች በፓይሬትድ (pirated) ሶፍትዌር (software) የሚሰሩ ከመሆናቸው አኳያ የበርን አባል መሆን ለሶፍትዌሮች በውጭ ምንዛሪ የሚከፈለው የክፍያ መጠን

ሶፍትዌር (በተለይም ማይክሮሶፍት ዊንዶውስ እና ሌሎች ምርቶች የሚሰሩ መሆኑ አይዘነጋም)። አገሪቱ ለትምህርት እና ለምርምር የምትጠቀማቸው መፃህፍቶች፣ ጆርናሎች እና ሌሎች ፅሁፎች ሁሉ ከንግዲህ እንደፈለጉ ኮፒ ማድረግ አይቻልም ማለት እንደሆነና እስካሁን ድረስ አንዴ ብቻ ለባለመብቱ ከፍለን እንደፈለግን ኮፒ ስናደረግ ቆይተናል። ወደ መዝናኛዎቹ ስንመለስም ሁላችንም እንደልብ ከያገሩ በመጡ ፊልሞችና ሙዚቃዎች ስንዝናና ቆይተናል ያለት ፅሁፍ አቅራቢው የበርን አባል ስንሆን ይህን ሁሉ እንከፍልበታለን ሲሉ ተደምጠዋል።

ከላይ እንደተገለፀው ገቢው ከወጪው ከበለጠ የበርን አባል መሆን ጥሩ ኢንቨስትመንት እንደሆነ ነገርግን የተገላቢጦስ ከሆነ ደግሞ ኪሣራ መሆኑን ገልፀዋል። በዚህ ዙሪያ ያሉ ሊተሬቸሮች እንደሚገልፁት ኔት ኢምፖርተርስ ለሆኑ አገሮች የበርን አባል መሆን መከራቸውን ሲያበዛና እና ባላንስ ኦፍ ትሬዳቸውን የባሰ ሲያናጋ (*ወይንም ከመግዛት እንዲቆጠቡ ሲያደርጋቸው*) ተስተዉሏል። ይህ አብዛኞቹን የአፍሪካ አገሮች ይመለከታል ብለዋል። የበርን ኮንቬንሽን international reciprocal arrangement ስለሆነ ኢትዮጵያ የምታገኘው ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያ እራሷ በእንካ ለእንካ መርህ የ166 ሀገራት ሥራዎችን ለመጠበቅ ግዴታ እየገባን መሆኑን ጠቁመው ጥያቄው ኔት የኮፒራይት importers ወይንስ exporters ነን የሚለው መሠረታዊ እንደሆነ አንስተዋል። ከአእምሯዊ ንብረት መብቶች ምርቶች በላይ ቡና እና የቆዳ ምርቶቻችን የሚበልጡብን መሆኑን የገለፁት አቶ አማን ቆዳና ቡና ደግሞ በአሁኑ ገበያ ዋጋቸው ፈፅሞ ከሶፍትዌር እና ከፊልም ጋር ሊወዳደሩአይችሉም ብለዋል። የኛ የአእምሮ ንብረት ገበያ ጥሩ ይሆናል ተብሎ የሚገመተው ኢትዮጵያዊያን በብዛት የሞኖሩባቸው እንደ አሜሪካ፣ ደ/አፍሪካ፣ እንግሊዝ እና መካከለኛው ምስራቅ ናቸው ብለዋል።

የበርን አባል መሆን እና የዉጭ ምንዛሬ ቁጥጥርስ እንዴት ይታያል የሚለውሌላው ነጥብ እንደሆነና ምናልባት የመጀመሪያ ክፍያ ከፍለን የምናመጣቸው የኮፒራይት ምርቶች ካስገባን በኋላ ተጨማሪ ኮፒዎች ይቅሩብን ካላልን (*እንደፈለግነው ኮፒ ማድረግ በበርን ምክንያት በፍቃዳችን ስለምንተው*) ለብዙዎቻችን የኮፒራይት ምርቶችን ለማስገባት የውጭ ምንዛሪ ከሚመለከተው አካል ልንፈልግ ነው ብለዋል። በውል ግዴታ ገብተው የበርንን ያክል ጥበቃ የተደረገላቸው (በርን አባል ሳንሆን ማለት ነው) ብዙ የውጭ አምራቾች/አቅራቢዎች እንደሚኖሩ አይካድም። አገሪቱም ለዚህ እየከፈለች ነው። ለምሳሌ በየባንኮቻችን የሚሰሩ ሶፍትዌሮች፣ በጉምሩክ፣ ግብር መስሪያ ቤት እና ሌሎችም ተቋማት ስራ የሚሰራባቸው እንደሚኖሩ አይካድም። የበርን አባል ስንሆን (ተጠቃሚነታችንን እስካላቆምን ድረስ) ወጪው

አሁን እየከፈልን ካለነው እጅግ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል የማያጠራጥር መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ጉዳዩ የግለሰብ ኩባንያዎች እንጂ የመንግስት አለመሆኑን መብቱ የተጣሰበት ሰው መጥቶ ክስ የሚመሰርት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በስራ ረገድ በመስኩ ላለን ሰዎች ትልቅ የስራ እና የጥቅም አጋጣሚ ሊሆን እንደሚችል የሚያጠራጥር ባይሆንም ካገር ጥቅም አኳያ ሲታይ ግን ገና ብዙ መታሰብ ያለበት ነጥብ አለ ብለዋል፡፡ በርን ለድሃ አገሮች የሚሰጣቸው በውስጡ የታቀፉ የላሉ አሰራሮች ያሉት መሆኑን የበርን አባሪ (appendix 3) ያለ መሆኑን ጠቁመው በ1971 የፓሪስ ሪቪዥን ላይም የተደነገገ መሆኑን፤ ይሁን እንጂ በበርካታ የጊዜ ገደቦች እና የእድሳት ጊዜዎች የታጠረ፣ የማሳወቅ ግዴታዎች ላይ የተመሰረተ፣ በርካታ የራሱ የሆኑ ልዩ ሁኔታዎች ያሉት (exceptions)፣ ለትምህርት እና ምርመር ብቻ የሚሰሩ ናቸው በማለት በዝርዝር አስረድተዋል፡፡



የመጀመሪያው ሃብታም አገሮች ውስጥ የታተሙትን የትምህርት ጽሑፎች ድሃ አገሮች ውስጥ ባሉ ዋና ዋና ቋንቋዎች እዲተረጎሙ የድሃ አገሩ መስተዳድር የሚፈቅድበት አሰራር ሆኖ ይህም ተፈፃሚ የሚሆነው በሃብታሙ አገር ዘንድ ከታተመ በኋላ ባሉት 3ት አመታት በድሃው አገር ዘንድ ካልተተረጎመ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ከሃብታሙ አገር የመጣው የመብቱ

ባለቤትእንዲተረጎም ፍቃደኛ ካልሆነ የሚሉ ልዩ ድንጋጌዎች የታጠረ መሆኑን ማሳያ ነው ብለው በምሳሌ አስረድተዋል፡፡ሁለተኛው የትምህርት ይዘት ያላቸውን ስራዎች ማባዛትን የሚመለከት ሲሆን ሃብታም አገሮች ዘንድ የሚታተሙ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ድሃ አገሮቹ ዘንድ ለአመታት  ያልቀረቡ መሆናቸው ተረጋግጦ ነው፡፡በተጨማሪ እነዚህ ልዩ ሁኔተዎች የሚሰሩባቸው የተንዛዙ ስነስርዓቶች መኖራቸውን ጠቅሰው ለምሳሌ ባለቤቱን መፈለግ፣ ማሳወቅ፣ ጊዜ መስጠት፣ ተመጣጣኝ ክፍያ መክፈል እና የመሳሰሉት ናቸው ብለዋል፡፡

የፓሪስ ኮንቬንሽን ለፓተንት፣ ለንግድ ምልክት፣ ለኢንደስትሪያል ዲዛይን፣ GIS፣ unfair competition ወዘተ ጥበቃ ያደርጋል፡፡ የበርን ስምምነት ትልቁ accomplishment National Treatment መሆኑን ጠቅሰው ፓተንት ለማግኘት በአንድ ሀገር apply ሲደረግ በሌሎች ሀገራት ደግሞ በ12 ወር ጊዜ ውስጥ apply መደረግ እንዳለበት፤ ኢንደስትሪያል ዲዛይን እና ለትሬድ ማርክ ደግሞ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ መሆን እንዳለበት የሚያስቀምጥ መሆኑ ገልፀዋል፡፡ የፓተንት መብትን ከሚያሰጡ ቅድመሁኔታዎች አንዱ novation መሆኑን ጠቅሰው ኮንቬንሽኑ መጀመሪያ ላስመዘገበ ሰው priority ይሰጣል ብለዋል፡፡ ከበርን በተቃራኒው የፓሪስ ኮንቬንሽን ብዙ ዝርዝር substantive ድንጋጌዎች የሉትም፡፡ ሀገራችን በኮፒ የምታስቸግር አለመሆኗንና ኮፒ ለማድረግም አቅም የሌለን መሆኑን ጠቅሰው ከበርን ኮንቬንሽን በተለየ መልኩ የፓሪስ ስምምነት ታዋቂ የሆኑ ሥራዎች እስኪመዘገቡ ጥበቃ የማይሰጥ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

## <u>አቶ ኤርሚያስ የማነብርሃን - አወያይ</u>

አቶ አማን አሠፋ ላቀረቡት እጅግ ሳቢ ለሆነው ፅሁፍ አቀራረብ ከልብ አመስግነው ‹‹Burn the Berne›› የሚል መፅሃፍ መኖሩን እና የመፅሃፉ ይዘትም የሀብታሞችን የሥራ ውጤት በድሃ ሀገራት ጥበቃ እንዲሰጣቸው ለማድረግ የተቀረፀ ነው ስለዚህ አቃጥሉት የሚል መልዕክት እንዳለው ለተሰብሳቢው አስረድተዋል፡፡

WIPO ለሃብታም ሀገራት ነው የቆመው የሚለውን ተከትሎ የባህላዊ እውቀቶች (traditional knowledge) ጥበቃ መስጠት እንደጀመረ የተናገሩት አወያዩ የአእምሯዊ ንብረት ጉዳይ የቴክኒክና የሕግ ጉዳይ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ የአእምሯዊ ንብረት ጉዳይ የእያንዳንዳችንን ሕይወት impact የሚያደርግ መሆኑን በማስረዳት በጠረጴዛችን ላይ ያለው የታሸገ ውሃ በራሱ በብዙ ዓይነት የአእምሮ ንብረት መብቶች የተሞላ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በመሆኑም የአእምሯዊ ንብረት መብት አለማቀፍ ስምምነት እና የሀገር ውስጥ ሕግጋት ድንጋጌዎችን በአግባቡ ማጤን ተገቢ እንደሆነ አስገንዝበው መድረኩን ለታሳታፊወች ጥያቄና አስተያየት  ክፍት አድርገዋል፡፡

## አቶ ኢሳያስ ይርጋ - ጠበቃ

በአዋጅ ቁጥር 410/96 መሠረት ጥያቄዎችን ያነሱ ሲሆን የመጀመሪያ ጥያቄያቸው አንድ የሕንድ ሙዚቀኛ መብቱ ሲጣስበት ካሳ የሚጠይቅ መሆኑ የተቀመጠ ሲሆን መብት የሚጥስ እና በወንጀል የሚያስጠይቅ ጥሰት ቢፈፅም በምን አግባብ ነው የሚጠየቀው የሚል ነጥብ አንስተዋል፡፡ ሌላው የፍ/ቤት ሥልጣንን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የፌደራል ስልጣን በሚሆንበት ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 25/88 መሠረት እንደሚጠየቀው የገንዘብ መጠን ፍ/ቤቱ የሚለይ ሲሆን የክልል ፍ/ቤቶች በውክልና ሲታይ በምን አግባብ እንደሆነ ጥያቄ አቀርበዋል፡፡ አክለውም በሶስተኛ ደረጃ የትርጉም ሥራዎች በበርን ኮንቬንሽን እንዴት እንደሚታዩ ለምሳሌ የቃና ቲቪን ጉዳይ አንስተዋል፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት በተከሰሰበት አንድ ጉዳይ ላይ የሰበር ችሎቱ የትርጉም ሥራ ጥበቃ አለው ብሏል ስለዚህ ኢትዮጵያ ፈራሚ አባል ሀገር ሳትሆን ይህ ጉዳይ በምን አግባብ ተግባራዊ እየሆነ ነው ያለው ሲሉ በመጨረሻም ባለ 3 ዳይሜንሽን ሥራዎች በሀገራችን ጥበቃ ይሰጣቸዋል ወይ በማለት ጥያቄያቸውን አንስተዋል፡፡

## አቶ መታሰቢያ ኃይሉ - የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር

የቀረበው ፅሁፍ እጅግ በጣም ግልፅ ሲሆን የበርን ኮንቬንሽንን ኢትዮጵያ ያላፀደቀችበት የፖሊሲ ምክንያት ምንድነው ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

## አቶ ፋሲል ስለሺ - ጠበቃ

የቀረበው ገለፃ እጅግ በጣም ጥሩ እንደሆነ ጠቅሰው ያወራነው ስለዓለምአቀፍ ሕግ ነው፡፡ ሀገራት ደግሞ የስምምነቱ ፈራሚ ሳይሆኑ በሕጉ ሊገዙና ሊገደዱ የሚችሉበትን አንድ አንድ ሁኔታዎች አሉ በዋናነት ሕጉ የinternational customary law status ካገኘ፡፡ ስለዚህ የበርን ኮንቬንሽን ብዙ ፈራሚ አባል ሀገራት ያሉት እጅግ የቆየ የአለምአቀፍ ሕግ እንደመሆኑ በstate practice ወደዚህ አስገዳጅነት እየመጣ አይደለም ወይ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

## <u>አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ፕሬዝዳንት</u>

የበርን ኮንቬንሽንን ወደ 197 ሀገራት የፈረሙ ሲሆን ቀሪ 29ኙ አልፈረሙም ስለዚህ ወደ customary international law እያደገ አይደለም ወይ የሚለውን የቀድሞው ጠያቂ አስተያየት በቁጥር አስደግፈው ያጠናከሩ ሲሆን በሌላ ጥያቄ ደግሞ የሌሎቹን ሀገር protect ከማድረግ የበለጠ አቅም ፈጥሮ ቢሰራ አይሻልም ወይ በፓሪስ ኮንቬንሽን ላይ ምክንያቱም የማኑፋክቸሪንግ አቅማችን ሲያድግ ኮፒ የማድረግ ፍላጎትና አቅም ይበልጥ ስለሚያድግ በማለት ጠይቀዋል፡፡

## <u>አቶ አማን አሠፋ - ጽሑፍ አቅራቢ</u>

በርን እና የወንጀል ሕጉ ግንኙነት የላቸውም በወንጀል የሚያስጠይቁ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የወንጀል ሕጉ ባስቀመጠው scope መሠረት የሚታይ እንደሆነ ገልፀው ባለ 3 ገፅታ ሥራዎችን አስመልክቶ (3D) የኢትዮጵያ የኮፒራይት ሕግ ጥበቃ የሚሰጥ ሲሆን በተለይም ሥነጥበባዊ ሥራዎች በሚል 3 ደይሜንሽናል ሥራዎች ጥበቃ ያገኛሉ ለምሳሌ claywork ን ጠቅሰዋል፡፡ የትርጉም ሥራን በሚመለከት ሥራ አመንጪው እንዲተረጎም የመፍቀድ ወይም ያለመፍቀድ መብት ያለው ሲሆን ከተተረጎመ በኋላ ተርጓሚው በderivative ሥራው ላይ መብት ይኖረዋል ያሉት ፅሁፍ አቅራቢው በርንን እስካሁን ያልፈረምንበት የኢትዮጵያ የፖሊሲ አቋምን በተመለከተ መረጃው የሌላቸው መሆኑንና የሚመለከተው የመንግሥት ኃላፊ በመካከላችን የሚገኙ በማሆናቸው ይህን ጉዳይ ሊያብራሩ የሚችሉ ስለመሆኑ ጠቁመዋል፡፡ የፓሪስ ስምምነትን መፈረም አያስጋንም ብለው እንደነበር እንደ ሀገር ፈጠራን በሚመለከት ፖሊሲ ሊኖረን እንደሚገባ የጠቀሱት አቶ አማን ከIP policy በፊት የinnovation policy ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ IP law must be economic instrument እንዲሁም ፈጠራን ማበረታታት አለበት ብለዋል፡፡ IP law is important for innovative wise society i.e. people capable of innovation but fear the act of copying. IP law is not important for dormant society. Copy የማድረግ አቅም የለንም old technology እንኳ ኮፒ ማድረግ አልቻልንም የኛ ሆቴሎች ወንበርና ጠረጴዛ ከውጭ ነው የሚያስመጡት በማለት ኮፒ በማድረግ ረገድ ኋላቀር መሆናችንን አንስተዋል፡፡ የፓሪስ ስምምነት አያስጋንም ያሉትም በዚሁ ምክንያት እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡



<u>አቶ ኤርሚያስ የማነብረሃን - አወያይ</u>

Trademark በኢትዮጵያ የተመዘገብ ባይሆንም ታዋቂ ከሆነ ጥበቃ ይደረግለታል ያሉት አወያዩ ጥቅም ላይ መዋልና ታዋቂ መሆን የተለያዩ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ ኮፒ ከማድረግ አቅም ጋር ተያይዞ ሥራዎችን መፍጠር የሚችሉ አሉ፤ መቅዳት የሚችሉ አሉ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ መሸከም የሚችሉ አሉ ያሉት አቶ ኤርሚያስ የአእምሮ መብት ጥበቃን እንደ መሣሪያ ነው የምናየው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ያለን ሲሆን የአእምሮ ንብረት ጥበቃደግሞ እውቅና በመስጠት የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያሳልጥትልቁ እና ወሳኝ መሣሪያ ነው፡፡ Process is patentable. Traditional knowledge and genetic resource በሕንድ ሀገር ጥረት ጥበቃ እንዲሰጠው የተደረገ የአእምሮ ንብረት መብት መሆኑን አውስተዋል፡፡ የአእምሮ ሃብት እጅግ በጣም ብዙ አለን ነገር ግን እነዚህን ሥራዎች ማስመዝገብ ላይ ትልቅ ውስንነት እንዳለ ጠቅሰው ለምሳሌ ሜቴክ ትራንስፎርመር እያመረተ ሲሆን ስለ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ እውቀት የለውም፡፡ የአእምሯዊ ንብረት ሕግ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ይበልጥ የሚያግዝ ነው፡፡

የፍ/ቤትን ጉዳይ በተመለከተ አቶ ኤርሚያስ ሲናገሩጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 12 በተወሰነ ውሳኔ መሠረት ከአእምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት ይግባኝ የሚሄደው ወደ ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን ጭምር ገልፀዋል፡፡ የፖሊሲ ጉዳይን በተመለከተ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት ክቡር አቶ አባይነህ በመካከላችን ስለሚገኙ የሚሉት ነገር ሊኖር ይችላል ሆኖም የአእምሯዊ ንብረት ረቂቅ ፖሊሲ መዘጋጀቱን አቶ ኤርሚያስ ጠቁመዋል፡፡ የአእምሯዊ ንብረት መብት ተፈፃሚነት በድንበር የታጠረ መሆኑን ገልፀው customary

international law በstate practice የሚመጣ ሲሆን የየትኞቹ ሀገራት ልማድ ነው ሕግ የሚሆነው ብለን ስንገመግም የሀብታምና ያደጉ ሀገራት እንጂ የደቡብ ሀገራትን አይወክልም ብለዋል፡፡

<u>አቶ አማን አሠፋ - ጽሑፍ አቅራቢ</u>

የበርን ስምምነት customary international law ስታተስ አላገኘም ፡፡ ይሄ የሚወሰነው በሀገራት ክርክር ሴቲንግ የሚነሳ እና የሚመጣ መሆኑን ጠቅሰው የአለም አቀቀፍ የልማድ ሕግ እንዲሆን የሚያስችል ክርክር ካለመኖሩም በላይ በበርን እና በፓሪስ ኮንቬንሽን መሠረት በሄግ አለምአቀፍ ፍ/ቤት ምንም ዓይነት ክርክር ባለመነሳቱ ስለዚህ ስታተስ ማውራት አስቸጋሪ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

<u>አቶ ተክላይ ተስፋይ</u>

የአለም አቀፍ የንግድ ድርጅት (WTO) አባልነት ከአእምሯ ንብረት ጋር ምን ያህል ተዛምዶ አላቸው ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

<u>አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር</u>

በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀፅ 36 ስር ስለ ወንጀል ኃላፊነት አስቀምጧል፡፡ በ1997 ሥራ ላይ በዋለው የወንጀል ሕግ መሻሻሉን ጠቅሰው በአዋጁ አንቀፅ 3 (2) መሠረት ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው ስምምነት ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ ተብሎ ተደንግጓል፡፡ስለሆነም ኢትዮጵያ የበርን ስምምነት ፈራሚ አባል ሀገር በትሆንና የሌሎች ሀገር ዜጎች የአእምሮ ንብረት መብቱን ቢጥሱ (infringe) ይጠየቃሉ በማለት በቀረበ ጥያቄ ላይ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

<u>አቶ አማን አሠፋ - ጽሑፍ አቅራቢ</u>

የአለም አቀፍ የንግድ ድርጅት አባል ስንሆን የTRIPS፣ የበርን እና የፓሪስ ስምምነቶች አውቶማቲካሊ ፈራሚ እንሆናለን፡፡ ነገር ግን በአለምአቀፍ የንግድ ድርጅት በኩል ያለው አካሄድ እጅግ ረዥም የሆነ negotiation የሚጠይቅ በመሆኑና grace periodየሚሰጥ በመሆኑ በቂ breathing space ይኖረናል ብለዋል፡፡

## ክቡር አቶ አባይነህ ተላከ - በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕ/ተ/ም/ቤትየሳይንስ መገናኛና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ

የሀገራችን ፓርላማ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው ካሏቸው ተግባራት መካከል የመጀመሪያው እና ዋናው ሕግ ማውጣት እንደሆነ ሌላው ወደ 18 በሚጠጉየፓርላማው ቋሚ ኮሚቴዎች አማካኝነት የሚመለከታቸውን ተጠሪ መሥሪያ ቤቶችን መከታተል ሌላው ሥራው መሆኑን፤ የሳይንስ፣ መገናኛ እና ቴክኖሎጂ ቋሚ ኮሚቴም ወደ 17 የሚሆኑ ተጠሪ መ/ቤቶች ያሉት ሲሆን የአእምሯዊ ንበረትጽ/ቤት አንዱ ነው ብለዋል፡፡

ከአእምሯዊ ንበረት ፖሊሲ በፊት የፈጠራ ፖሊሲ የሚያስፈልገን መሆኑ እሙን መሆኑን የጠቀሱት ክቡር አቶ አባይነህ የፈጠራ ፖሊሲ ያለን መሆኑን ለቤቱ አስገንዝበዋል፡፡ የተለያዩ ሀገራት በተለይ ጃፓን ኮፒ በማድረግያደጉ ስለመሆናቸው ጠቅሰው ኮፒ ስናደርግ 1ኛ በመምረጥ፣ 2ኛ በማላመድ እንዲሁም 3ኛ በማሰራጨት መሆን እንደሚገባ ገልጸው የሀገራችን ብዙ ሃብት በተለይም የባሕላዊ እውቀቶችን እየተዘረፍን መሆኑ ሊጤን እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

## አቶ ኤርሚያስ የማነብርሃን - አወያይ

ፅሁፍ አቅራቢውን አቶ አማን አሠፋን፣ ተሳታፊዎችን እንዲሁም የመወያያ መድረኩን ያዘጋጀውን የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያዎች ማኀበርን ከልብ በማመስገን መድረኩን ለማኀበሩ ፕሬዝዳንት አቶ ቴዎድሮስ አስረክበዋል፡፡

## አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - የኢ/ሕ/ባ/ማኀበር ፕሬዝዳንት

የቀረበው የመወያያ ጽሑፍ እጅግ ማራኪና ጥሩ እንደነበረ በመግለፅ ጽሑፍ አቅራቢው አቶ አማን አሠፋ ጽሑፉን ከማቅረብ ባሻገር የፕሮግራሙን ወጭ በመሸፈን ለማኀበሩ እገዛ ያደረገ በመሆኑ በድጋሚ ሊመሰገን እንደሚገባ እና አቶ ኤርሚያስ የማነብርሃንም ያላቸውን የተጣበበ ጊዜ መሰዋዕት በማድረግ በአወያይነት ተሳታፊ በመሆናቸው ያላቸው አክብሮት የገለፁ ሲሆን የሳይንስ መገናኛና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ክቡር አቶ አባይነህ ተላከ እንዲሁም የመድረኩ ተሳታፊዎች በሙሉ ጥሪያችንን አክብራችሁ ስለተገኛችሁ በማህበሩ እና በራሳቸው ስም ምስጋና አቅርበው ውይይቱ ከቀኑ 6፡30 ላይ ተጠናቋል፡፡

///////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////